መልእክት ሦስት

## ቀኑ እስኪጠባ ድረስ፣ የንጋትም ኮከብ በልባችን እስኪወጣ ድረስ፣ በጨለማ ስፍራ ለሚበራ መብራት ጥንቃቄ እንደሚደረግ ለትንቢቱ ቃል በመጠንቀቅ ለጌታ መምጣት ራሳችንን ዝግጁ ማድረግ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 2 ጴጥ. 1፡19፤ መዝ. 119፡105፣ 130፤ ራእ. 2፡28፤ ሚል. 4፡2፣ 1 ተሰ. 5፡4-6

**I. ለትንቢቱ ቃል መጠንቀቅ ለአማኞች ወሳኝ ነገር ነው—2 ጴጥ. 1፡19፦**

ሀ. ትንቢቶች እግዚአብሔር እንድናውቃቸው የሚፈልጋቸው ጉዳዮች ናቸው፣ አማኞችም ለእነርሱ መጠንቀቅ አለባቸው—1 ጴጥ. 1፡10፣ 2 ጴጥ. 3፡2፤ ሉቃ. 1፡70።

ለ. ጌታ ኢየሱስ ትንቢቶችን እንድናስተውል አዝዞናል፤ ይህ አማኞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላሉት ትንቢቶች ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው በግልጽ ያሳያል—ማቴ. 24፡15፣ ተዛ. ዳን. 9፡24-27።

ሐ. ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ ትንቢቶች በቂ ትኩረት ካልሰጠች፣ ከዚያ እውቀት እጥረት የተነሣ ብዙ አማኞች እምነት ማጣታቸው፣ በውሸቶች መታለላቸው፣ መጥፋታቸው እና ነቅተው የሚጠብቁ ባለመሆን የጌታን መምጣት መርሳታቸው የማይቀር ነው—ሆሴ. 4፡6፤ 1 ተሰ. 5፡4-6፤ ማቴ. 24፡42፤ 1 ጴጥ. 5፡8።

መ. አማኞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ትንቢቶች ከሌሏቸው፣ ወደ ጨለማ ውስጥ ይወድቃሉ—ሐዋ. 26፡18፤ ዮሐ. 12፡35-36፤ ኤፌ. 5፡8-9፦

1. የአሁኑ ዘመን ሌሊት ነው—ሮሜ 13፡12፤ 1 ተሰ. 5፡4-8።
2. ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ፣ ቀኑ ይጠባል (2 ጴጥ. 1፡19)፣ ቀጣዩ ዘመን፣ የመንግሥቱ ዘመን፣ ቀን ይሆናል።

**II. ጴጥሮስ በቅዱሳት መጻሕፍት ያለውን የትንቢቱን ቃል በጨለማ ስፍራ ከሚበራ መብራት ጋር ያመሳስለዋል—ቁ. 19፦**

ሀ. ይህ የሚያመለክተው ይህ ዘመን በጨለማ ሌሊት ውስጥ ያለ ጨለማ ስፍራ እንደሆነ (ሮሜ 13፡12)፣ የዚህም ዓለም ሰዎች በሙሉ በጨለማው ውስጥ እየተንቀሳቀሱ እና እየሠሩ እንዳሉ ነው (ተዛ. ሐዋ. 26፡18)።

ለ. ለአማኞች እንደሚያበራ መብራት የሆነው የቅዱሳት መጻሕፍት የትንቢቱ ቃል የጌታ መገለጥ ቀን እስኪጠባ ድረስ፣ በጨለማው ሌሊት ለማለፍ እንኳን ሳይቀር ብሩህ ወደሆነ ቀን የሚመራቸው (ለአእምሮአቸው መረዳት ብቻ የሆነ የፊደል እውቀትን ሳይሆን) በጨለማቸው ላይ የሚያበራ መንፈሳዊ ብርሃንን ያስተላልፋል—2 ጴጥ. 1፡19፤ 2ጢሞ. 4፡8፤ 1፡12።

ሐ. ጌታ እንደ ፀሐይ ብርሃን ከመገለጡ በፊት፣ ይህ ቃል እንደ ብርሃን በእርምጃዎቻችን ላይ ሊያበራ ያስፈልገናል—ሚል. 4፡2፤ መዝ. 119፡105፣ 130።

መ. በጨለማ ስፍራ እንደ መብራት ለሚያበራው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላለው የትንቢት ቃል ከተጠነቀቅን፣ በጨለማው ላይ ለማብራት ክርስቶስ በልባችን ውስጥ ይወጣል—2 ጴጥ. 1፡19።

**III. ቀኑ እስኪጠባ ድረስ፣ የንጋትም ኮከብ በልባችን እስኪወጣ ድረስ፣ በጨለማ ስፍራ ለሚበራው መብራት መጠንቀቅ ያስፈልገናል—ቁ. 19፦**

ሀ. "የጨለማ ስፍራ" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል "ጨለማ የሆነ ስፍራ"፣ በጣም ቆሻሻ፣ ደረቅ እና ችላ የተባለ ስፍራ ተብሎም ሊተረጎም ይችላል።

ለ. *ቀኑ* የሚለው ቃል፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ላለው የሚያበራ ቃል በመጠንቀቅ እንዲያበሩ በተደረጉት እና አብርሆት በተሰጣቸው በቅዱሳን ልብ ውስጥ ከመውጣቱ በፊት፣ እየወጣ ካለ የንጋት ኮከብ ጋር እንደሚጠባ ብሩህ ቀን በብርሃን የተሞላ የሚመጣን ጊዜ የሚያሳይ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው፦

1. ይህ አማኞች የጌታን መገኘት ከልባቸው እንዲፈልጉ እና ጌታ እንደ ሌባ ሲመጣ፣ ምሥጢራዊ በሆነው የመምጣቱ (ፓሮዚያ) ክፍል ጌታን እንዳያጡት ነቅተው የሚጠብቁ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፣ ያበረታታቸውማል—ማቴ. 24፡27፣ 42-43፣ 2 ተሰ. 2፡8።
2. ይህ ዘይቤያዊ አገላለጽ፣ ብርሃኑ የዚህን ዘመን ጭጋጋማ የጨለማ ሌሊት ለመስበር በሚያበራው፣ በጌታ እንደ የጽድቅ ፀሐይ መገለጥ (መምጣት) እንደ ቀን የሚጠባውን፣ የሚመጣውን ዘመን፣ የመንግሥቱን ዘመን ማመልከት አለበት—ማቴ. 4፡2።

ሐ. የንጋት ኮከቡ፣ ቀኑ ከመጥባቱ አስቀድሞ በጨለማው ሰዓት ይገለጣል—ራእ. 22፡16፣ ተዛ. ዘኍ. 24፡17፤ ማቴ. 2፡2፣ 9-10፡-

1. ይህ የሚያመለክተው ክርስቶስ ከዚህ ዘመን መጠናቀቅ አስቀድሞ እንደብሩሁ የንጋት ኮከብ በጨለማው ሰዓት እንደሚገለጥ ነው—ራእ. 22፡16።
2. የጌታ እንደ የንጋት ኮከብ መገለጥና እንደ የጽድቅ ፀሐይ መገለጥ በተመሳሳይ ጊዜ አይሆንም—2፡28፣ ሚል. 4፡2፡-
   ሀ. የንጋት ኮከቡ የሚገለጠው ቀኑ ከመጥባቱ በፊት ነው፣ የፀሐይ መውጣት ደግሞ የሚከሰተው ከቀኑ መንጋት በኋላ ነው።
   ለ. ከቀኑ መጥባት በኋላ እንደ የጽድቅ ፀሐይ ክርስቶስ በምድር ላሉት ሕዝብ በሙሉ በገሃድ ይገለጣል—ቁ. 2።
   ሐ. ከቀኑ መጥባት በፊት እንደሚያበራው የንጋት ኮከብ፣ ነቅተው ለሚጠባበቁት፣ ለተዘጋጁት እና እርሱን ለሚጠብቁት ድል ነሺዎች በግል ይገለጥላቸዋል—ራእ. 22፡16።
   መ. ከረጅም ቆይታ በኋላ ሲመጣ የመገኘቱን ትኩስነት ይቀምሱ ዘንድ ቅድሚያውን እንዲያገኙ ለሚወዱትና ነቅተው ለሚጠባበቁት ራሱን እንደ ንጋት ኮከብ በምሥጢር ይሰጣቸዋል—2፡28።

መ. በጨለማ ስፍራ ለሚበራ መብራት ጥንቃቄ እንደሚደረግ ለቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ስንጠነቀቅ፣ በውስጣችን የሚኖረው ሁኔታ እየጠባ እንዳለ ቀን እና የንጋት ኮኮብ በልባችን እንደሚወጣ አይነት ይሆናል—2 ጴጥ. 1፡19፡-

1. በስእላዊ አገላለጽ *ቀኑ እስኪጠባ* የሚለው እንደሚጠባ ብሩህ ቀን የሚመጣውን የመንግሥቱን ዘመን ያመለክታል—ተዛ. ማቴ. 13፡43።
2. የክርስቶስን ምሳሌዎች በተመለከተ፣ መላው መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ እንደ ብርሃን ይጀምርና በእርሱ እንደ ንጋት ኮከብ ያጠናቅቃል—ዘፍ. 1፡3፣ ራእ. 2፡28፣ 22፡16።
3. *የንጋት ኮከብ*፣ በሌሊቱ የጨለማው ክፍል፣ የመንግሥቱ ዘመን ከመምጣቱ አስቀድሞ፣ መገለጡን ለሚወዱ በምሥጢር በልባቸው የሚወጣውን ክርስቶስ ያመለክታል—ቁ. 16።
4. በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ላለው ለሚያበራው ቃል ያለማቋረጥ ከተጠነቀቅን፣ በውስጣችን እንደሚጠባ ቀን መንግሥቱ፣ እንደሚያበራው የንጋት ኮከብ ከመገለጡ በፊት በልባችን እንደሚወጣው እንደሚያበራው የንጋት ኮከብ ክርስቶስ ይኖረናል—2 ጴጥ. 1፡19፣ ራእ. 2፡28።
5. ክርስቶስ እንደ ንጋት ኮከብ ለድል ነሺዎቹ እንደመጀመሪያ ሽልማታቸው ይሰጣቸዋል፣ እንደ ንጋት ኮከብ ለሆነው የጌታ ምሥጢራዊ መገለጥ ራሳችንን ዝግጁ ማድረግ አለብን—ቁ. 28-29።

*© 2023 Living Stream Ministry*